# ቡሳ ጎኖፋ
# ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር

## የተሻሻለ የመመስረቻ ጽሁፍ

ሰኔ 3 ቀን 2015

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

# ቡሳ ጎኖፋ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር
# የተሻሻለ የመመስረቻ ጽሁፍ

## አንቀጽ 1
## መቋቋም

እኛ ከዚህ በታች ስማችን ፣ ዜግነታችን ፣ አድራሻችንና ፊርማችን የተገለፀው መስራች አባላት በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ እና በዚህ የመመስረቻ ጽሁፍ የማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር ያቋቋምን ሲሆን በአዲሱ የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 መሰረት የማህበሩን የመመስረቻ ጽሁፍ እንደሚከተለው አሻሽለናል።

## አንቀፅ 2
## የማህበሩ ስም፣ ዋና መስሪያ ቤት እና አድራሻ፣

1. ቡሳ ጎኖፋ ማይክሮ ፋይናንስ አ.ማ. ተብሎ ይጠራል።
2. የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ከተማ ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 02/03 የቤት ቁጥር 312 ነው።
3. ማህበሩ እንደ አስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ መ/ቤቶችን በተለያዩ ክልሎች ላይ ሊያቋቁም ይችላል።

## አንቀፅ 3
## መስራች አባላት፣ ዜግነት፣ አድራሻና የአክሲዮን መጠን፤

የማህበሩ መስራች አባላት፣ ዜግነት፣ አድራሻና ያላቸው የአክሲዮን መጠን እንደሚከተለው ነው።

| ተ.ቁ | የባለአክስዮን ስም | አድራሻ | ዜግነት | የአክሲዮኖች ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የተፈረመ አክስዮን | በጠቅላላ የተከፈለ አክስዮን (ብር) | የአክሲዮን ድርሻ |
| 1 | ሁንዴ- ኦሮሞ ግራስሩትስ ዴቬሎፐመንት ኢኒሼቲቭ | አ.አ ቂርቆስ ክ/ከ ወ-03 የቤ.ቁ 354 | ኢትዮ | 19,626 | 1,962,600.00 | 19.63% |
| 2 | አቶ አለማየሁ ዲሮ ለሊሴ | አ.አ ቦሌ ክ/ከ ወ-04 የቤ.ቁ 335 | " | 18,692 | 1,869,200.00 | 18.69% |
| 3 | አቶ አሸብር ከበደ ነገሮ | አ.አ ቂርቆስ ክ/ከ ወ-04 የቤ.ቁ 1080 | " | 467 | 46,700.00 | 0.47% |
| 4 | ወ/ሮ ደራርቱ አባነጋ ሰዲቅ | አ.አ ወ-18 ቀ-26 የቤ.ቁ 332/21 | " | 467 | 46,700.00 | 0.47% |
| 5 | አቶ ደረጀ ካሳ አብዲ | ኦሮሚያ ሞጆ ቀ-02 የቤ.ቁ 2118 | " | 467 | 46,700.00 | 0.47% |
| 6 | ዶክተር ገመቹ መገርሳ ሩዳ | አ.አ ወ-14 ቀ-07 የቤ.ቁ C-201 | " | 18,692 | 1,869,200.00 | 18.69% |
| 7 | ወ/ሮ ገነት ታደሰ ዱባለ | አ.አ ወ-16 ቀ-22 የቤ.ቁ አዲስ | " | 192 | 19,200.00 | 0.19% |
| 8 | ወ/ት ቀንቢ ኩምሳ ቦሮ | አ.አ ወ-08 ቀ-11 የቤ.ቁ 785 | " | 467 | 46,700.00 | 0.47% |
| 9 | አቶ መንግስቱ ያዕቆብ ጉደታ | አ.አ ቦሌ ክ/ከ ወ-10 የቤ.ቁ 202A | " | 234 | 23,400.00 | 0.23% |
| 10 | ወ/ሮ ሽምሲያ አስማን መሐመድ | አ.አ ንፋስ/ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ወ-12 የቤ.ቁ 3905 | " | 467 | 46,700.00 | 0.47% |
| 11 | አቶ ሶርሳ ደበላ ገላልቻ | አ.አ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ቡራዩ ቀ-ቡራዩ ከታ የቤ.ቁ 4937 | " | 467 | 46,700.00 | 0.47% |
| 12 | አቶ ተርፌሳ ደንደና ጉተማ | አ.አ ቦሌ ክ/ከ ወ-05 የቤ.ቁ 1506 | " | 467 | 46,700.00 | 0.47% |
| 13 | አቶ ተስፋዬ ደስታ ክ/ሚካኤል | አ.አ ቂርቆስ ክ/ከ ወ-05 የቤ.ቁ አዲስ | " | 467 | 46,700.00 | 0.47% |
| 14 | አቶ ተሾመ ዮሐንስ ደዬሶ | አ.አ አቃቂ-ቃሊቲ ክ/ከ ወ-01 የቤ.ቁ 772 | " | 18,692 | 1,869,200.00 | 18.69% |
| 15 | ወ/ት ትዕግስት ታደሰ ዱባለ | አ.አ ወ-20 ቀ-42 የቤ.ቁ 257 | " | 234 | 23,400.00 | 0.23% |
| 16 | አቶ ዘገየ አስፋው አብዲ | አ.አ ቦሌ ክ/ከ ወ-03 የቤ.ቁ 207 | " | 19,626 | 1,962,600.00 | 19.63% |
| 17 | አቶ እንዳለ ፎዩ ጂሩ | አ.አ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ቡራዩ ቀ-ለኩ ከታ 02 የቤ.ቁ 8625 | " | 138 | 13,800.00 | 0.14% |
| 18 | አቶ ሰለሞን ማሞ አረዶ | አ.አ ንፋስ/ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ወ-01 የቤ.ቁ አዲስ | " | 138 | 13,800.00 | 0.14% |
| | ጠቅላላ ድምር | | | 100,000 | 10,000,000.00 | 100% |

# አንቀፅ 4

## የማህበሩ አላማዎች

የማህበሩ አላማዎች የሚከተሉት ይጨምራል፡፡

1. በገጠርና በከተማ፣ በግብርና በጥቃቅንና አነስተኛ እንዲሁም ሌሎች መሰል የሥራ መስኮች ላይ ለተሰማሩ ገበሬዎች፤ሴቶች፤ወጣቶች፣ ኢንተርፕራይዞች፣ ማህበራት ወይም ለህብረት ስራ ማህበራት አነስተኛ ብድር ማቅረብ፤
2. የወጼታም ሆነ የግደታ ቁጠባ፤ በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈል ቁጠባን እንዲሁም የጊዜ ገደብ ተቀማጭን መቀበል፤ በተጨማሪም ቁጠባን ማበረታታት፤
3. በአገሪቱ ውስጥ የሚከፈሉ የሃዋላ ሰነዶችን ማዉጣትና መቀበል፤
4. በአገሪቱ ውስጥ የሚከናወኑ የሃዋላ አገልግሎቶችን መስጠት፤
5. ገቢ የሚያስገኙ የመንግስት የግምጃ ቤት ሰነዶችን ጨምሮ የገንዘብ ሰነዶችን መግዛት፤
6. ለቢሮና ለተለያዩ አገልገሎት የሚዉሉ ህንጻዎችን ጨምሮ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ማፍራት፣ በይዞታ ስር ማስቀረትና ማስተላለፍ፤
7. ለለገጠርና ለከተማ አነስተኛ አምራቾችና አገልግሎት ሰጪዎች ገቢ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶችን ማበረታታት፤
8. ለተበዳሪዎች እንደ የአስፈላጊነቱ የገንዘብ አያያዝ፣የሥራ አመራር፣ የገበያ፣ የቴክኒክና አስተዳደር ምክር አገልግሎት መስጠት ወይም አገልግሎቱን እንዲያገኙ ድጋፍ መስጠት፤
9. ብሔራዊ ባንክ በየጊዜዉ በሚያወጣቸው መመሪያዎች የሚወሰኑ ሌሎች ሥራዎች ላይ ይሰማራል /ይሰራል/፡

# አንቀፅ 5

## የማህበሩ ካፒታል እና የአክሲዮን መጠን

1. የማህበሩ የተፈረመ ካፒታል ብር 10,000,000.00 (አስር ሚሊዮን ብር) ነው፡፡
2. ይህ የተሻሻለው የመመስረቻ ፅሁፍ በተፈረመበት ጊዜ የማህበሩ ካፒታል ሙሉ ለሙሉ የተከፈለ ሲሆን የማህበርተኞቹ የአክሲዮን ድርሻ መጠን እንደሚከተለው ነው፣

| ተ.ቁ | የባለአክስዮን ስም | የአክሲዮን ብዛት | የአንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሁንዴ- ኦሮሞ ግራስሩትስ ዴቬሎፐመንት ኢኒሼቲብ | 19,626 | 100 | 1,962,600.00 |
| 2 | አቶ አለማየሁ ዲሮ ለሊሴ | 18,692 | 100 | 1,869,200.00 |
| 3 | አቶ አሸብር ከበደ ነገሮ | 467 | 100 | 46,700.00 |
| 4 | ወ/ሮ ደራርቱ አባነጋ ሰዲቅ | 467 | 100 | 46,700.00 |
| 5 | አቶ ደረጀ ካሳ አብዲ | 467 | 100 | 46,700.00 |
| 6 | ዶክተር ገመቹ መገርሳ ሩዳ | 18,692 | 100 | 1,869,200.00 |
| 7 | ወ/ሮ ገነት ታደሰ ዱባለ | 192 | 100 | 19,200.00 |
| 8 | ወ/ት ቁንቢ ኩምሳ ቦሮ | 467 | 100 | 46,700.00 |
| 9 | አቶ መንግስቱ ያዕቆብ ጉደታ | 234 | 100 | 23,400.00 |
| 10 | ወ/ሮ ሽምሲያ አስማን መሐመድ | 467 | 100 | 46,700.00 |
| 11 | አቶ ሶርሳ ደበላ ገላልቻ | 467 | 100 | 46,700.00 |
| 12 | አቶ ተርፌሳ ደንደና ጉተማ | 467 | 100 | 46,700.00 |
| 13 | አቶ ተስፋዬ ደስታ ክ/ሚካኤል | 467 | 100 | 46,700.00 |
| 14 | አቶ ተሾመ ዮሐንስ ደዬሶ | 18,692 | 100 | 1,869,200.00 |
| 15 | ወ/ት ትዕግስት ታደሰ ዱባለ | 234 | 100 | 23,400.00 |
| 16 | አቶ ዘገየ አስፋዉ አብዲ | 19,626 | 100 | 1,962,600.00 |
| 17 | አቶ እንዳለ ፎዬ ጂሩ | 138 | 100 | 13,800.00 |
| 18 | አቶ ሰለሞን ማሞ አረዶ | 138 | 100 | 13,800.00 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **100,000** | | **10,000,000.00** |

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

## አንቀፅ 6
## የአባላት መብቶች እና ግዴታዎች

ማንኛውም አባል የሚከተሉት መብቶች እና ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1. በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የመሳተፍና ድምፅ የመስጠት፣
2. የማኅበሩን የሒሳብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎች፤ በዲሬክተሮች ቦርድና በኦዲተሮች ለጠቅላላ ጉባኤ የቀረቡ ሪፖርቶችን የማየት እና ቅጂዎችን የመውሰድ መብት፤
3. የማህበሩ የጠቅላላ ጉባዔ ቃለ ጉባኤዎችንና በጉባኤው የተሳተፉ ባለአክሲዮኖችን መመዝገቢያ ሰነድ ጠይቆ የማግኘት፤
4. ከማህበሩ ከተጣራ ዓመታዊ ትርፍ እንዲሁም ማህበሩ ሲፈርስ ከሚቀረዉ የተጣራ ንብረት በያዘዉ አክሲዮን መሰረት ድርሻ የማግኘት፤
5. ማህበሩን በተመለከተ የጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጠውን ውሣኔና በዲሬክተሮች ቦርድ የሚሰጠውን የአፈጻጸም ውሣኔዎችን የመፈፀም ግዴታ አለባቸዉ፡፡

## አንቀፅ 7
## የአክሲዮኖች ምዝገባ

1. ማህበሩ አንድ አይነት ደረጃ ያላቸውና መደበኛ ዋጋቸው ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) የሆነ 100,000/ አንድ መቶ ሺህ/ አክሲዮኖች ይኖሩታል፡፡
2. አክሲዮኖች በእያንዳንዱ አባል ስም የሚመዘገቡ ይሆናል፡፡ ለአምጪው የሚባሉ አክሲዮኖች የተከለከሉ ናቸው፡፡
3. አክሲዮኖች የማይከፋፈሉ ሆነው በአንድ አባል የሚያዘው ዝቅተኛው የአክሲዮን ብዛት አንድ ይሆናል፡፡
4. የባለአክሲዮኖቹን ዝርዝር የሚያመለክት መዝገብ በማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ይቀመጣል፡፡ ይህ መዝገብ የባለአክሲዮኖቹን ስምና እያንዳንዱ አባል ያለውን የአክሲዮን መጠን በትክክል የተመዘገበዉን ያመለክታል፡፡ በመዝገቡ ውስጥ ስህተት ቢኖር /መኖሩ በተረጋገጠ/ በ30 ቀናት ውስጥ ታርሞ ይመዘገባል፡
5. የአክሲዮን መዝገቡ ዝርዝር በትክክል ባለመጻፉ ምክንያት ለሚደርሰዉ ማንኛውም ጉዳት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በአንድነትና በተናጠል ሃላፊዎች ይሆናሉ፡፡

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

## አንቀፅ 8
## የባለአክሲዮንነት ሰርተፊኬትና የጠፉትን አክሲዮኖች ስለመተካት

1. ማህበሩ ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን በስሙ የተመዘገበ፣ የአክሲዮን ብዛትና መጠን የሚገልጽ የባለአክሲዮንነት ማረጋገጫ ሴርቴፍኬት ይሰጣል፡፡
2. የባለአክሲዮኖቹ ሰርተፊኬቶች ከጠፉ፣ ካረጁ ወይም በማናቸውም መንገድ ከተበላሹ ከዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት በባለአክሲዮኖቹ ወጪ እንዲተካ ይደረጋል፡፡

## አንቀፅ 9
## አክሲዮን የማስተላለፍ መብት

1. ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት የማህበሩ ባለአክሲዮን መሆን ይችላል፡፡
2. ድርሻውን በከፊል ወይም በሙሉ ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ የፈለገ ባለአክሲዮን ይህንኑ በፅሁፍ ለዋና ስራ አስኪያጅ ማሳወቅ አለበት፡፡ ዋና ስራ አስኪያጁም የአክሲዮን ማስተላለፉን ጥያቄ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አቅርቦ ውሣኔ እንዳሲጠበት ያደርጋል፣
3. ዋና ሥራ አስኪያጁ የአክሲዮን ማስተላለፉ ውሣኔ ከዳይሬክተሮች ቦርድ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ አክሲዮኑን በመደበኛ ወይም በተጻፈዉ ዋጋ (ፓር ቫልዩ) ለሌሎች የማህበሩ ባለአክሲዮኖች በሚከተለው ቅደም ተከተል መሰረት ይሸጣል፡

   ሀ/ አነስተኛ መጠን አክሲዮን ላላቸው ባለአክሲዮኖች፣

   ለ/ በእጣ ፈቃደኛ ለሆኑ አባላት፣

   ሐ/ ለቡሳ ጎኖፋ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር ይሸጣል፡፡
4. አክሲዮን ማህበሩ የራሱን አክሲዮኖች ከአባላቱ መልሶ መግዛት ይችላል፣ ለግዥዉ የሚደረገዉ ክፍያም ከማህበሩ የተጠራቀመ ትርፍ እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ሥር በተገለጹት ሁኔታዎች ከአንዱ ባለአክሲዮን ወደሌላዉ ባለአ□ሲዮን የተላለፈ አክሲዮን በማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኘዉ የባለአሲዮኖች መዝገብ ዉስጥ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡
6. በተጨማሪም ስም የተጻፈባቸዉ አክሲዮኖች ወደ ሌላ ሰው የሚተላለፉት አክሲዮኑን በመስጠትና በማህበሩ የባለአክሲዮኖች መዝገብ አክሲዮን በተላፈለት ሰው ስም በማስመዝገብ ብቻ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 10
### የባለ አክሲዮኖች ኃላፊነት

በህግ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ከማህበሩ እዳ ጋር በተያያዘ የባለአክሲዮኖች ተጠያቂነት አባላቱ በማህበሩ ውስጥ ባላቸው የአክሲዮን መጠን ብቻ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 11
### የትርፍ አከፋፈል

1. የማህበሩ የተጣራ ትርፍ ማለት በየዓመቱ የትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ መሰረት ከመደበኛ እንቅስቃሴዎች ከመነጩት ገቢዎች ላይ ጠቅላላ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚገኘዉ ትርፍ ነዉ።
2. ከማህበሩ የተጣራ ትርፍ ላይ የካፒታሉን ሀምሳ በመቶ (50%) እስኪደርስ ድረስ በየዓመቱ ሃያ አምስት በመቶ (25%) እየተቀነሰ በህጋዊ መጠባበቂያ ገንዘብ ይያዛል።
3. ከላይ በተራ ቁጥር 2 የተመለከተዉ ቢኖርም ለማህበሩ የተደራሽነት ዓላማ ማስፈፀሚያ የሚዉል የተለየ መጠባበቂያ ገንዘብ (ልዩ ፈንድ) ከተጣራዉ ትርፍ ላይ በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ዉሳኔ መሰረት ይያዛል፡፡ መጠኑም በጠቅላላ ጉባዔ የሚወሰን ይሆናል፡፡
4. በተራ ቁጥር 2 እና 3 ላይ የተጠቀሰዉ ከተቀነሰ በኋላ ቀሪዉ የተጣራ ትርፍ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሚወስነው መሰረት እንደአስፈላጊነቱ ማህበሩ በሙሉም ሆነ በከፊል የባለአክሲዮኖችን የተከፈለ ካፒታል ሊያሳድግበት ወይም ወደ መጠባበቂያ ገንዘብ በማዞር ለስራ ማስፋፊያነት ሊያዉለዉ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 12
### የማህበሩ አመራር አካላት

1. ማህበሩ የሚከተሉት የሥራ አመራር አካላት ይኖሩታል፡
   ሀ/ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ
   ለ/ የዳይሬክተሮች ቦርድ
   ሐ/ ዋና ሥራ አስኪያጅ
   መ/ ኦዲተር
   ሠ/ የማህበሩ ፀሐፊ
2. የጠቅላላ ጉባኤው፣ የዋና ስራ አስኪያጁና የኦዲተር ሥልጣንና ኃላፊነት በሀገሪቱ ህግና በመመስረቻ ጽሁፉ ላይ በተመለከተው ይሆናል፡፡

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

## አንቀፅ 13

## የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ እና የአጠራር ሁኔታ

1. የባአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚሳተፉበት የማህበሩ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጭ አካል ነው፡፡
2. የባአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ ወይም አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
3. የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ ጥሪ በዳይሬክተሮች ቦርድ፣በፍ/ቤት ውሳኔ እና በሂሳብ አጣሪዎች ሊጠራ ይችላል፡፡
4. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ለስብሰባው ከተቆረጠው ቀን 24 ቀናት አስቀድሞ በጋዜጣ በሚወጣ ማስታወቂያ፣በሪኮማንዴ በሚላኩ ደብዳቤዎች፣በኢሜይል ወይም ሌላ አስተማማኝ የኤለክትሮኒክ ዘዴ ይጠራል፡፡

## አንቀፅ 14

## መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ

1. የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሂሳብ ዓመቱ ከተዘጋበት ቀን ጀምሮ ባለት ስድስት ወራት ውስጥ ይደረጋል፡፡
2. በመጀመሪያው የመደበኛ ጠ/ጉባኤ ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የዋና ገንዘብ /ካፒታል/ አንድ አራተኛ (¼ኛ) የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸዉ ከተገኙ ጉባኤውን ማካሄድና ውሣኔ ማሳለፍ ይቻላል፡፡
3. በሁለተኛው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖችን የሚወክሉ ዋና ገንዘብ /ካፒታል/ ግምት ውስጥ ሳይገባ በተገኙት አክሲዮኖች ጉባኤ ማካሄድና ውሣኔ ማሳለፍ ይቻላል፡፡
4. ውሣኔዎች የሚተላለፉት በጉባኤው ከተገኙት ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸዉ አክሲዮኖች አብዛኛውን ካፒታል በሚወክሉት ድምጽ ከተደገፈ ነው፡፡

## አንቀፅ 15

## የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡

1. የማህበሩን የሀብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎችን እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት እና የዉጭ ኦዲተሮች የኦዲት ሪፖርት በመመርመር ያፀድቃል፡፡
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን እንዲሁም የዉጭ ኦዲተሮችን ይሾማል፣ ይሽራል፣ ክፍያቸውንም ይወስናል፡፡

3. በዳይሬክተሮች ቦርድና በኦዲተሮች ሪፖርት ውስጥ በተነሱት ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. በማንኛውም ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች እንዲሁም የትርፍ አከፋፈልን፣ እና ካለፈው በጀት ዓመት ሂሳብ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፡፡
5. ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ተለይተው ያልተሰጡ ሌሎች ጉዳዮችን መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 16

## አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ

1. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በዳይሬክተሮች ቦርድ፣በፍ/ቤት ውሳኔ እና በሂሳብ አጣሪዎች በማንኛውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል፡፡
2. የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የመጀመሪያ ስብሰባ ምልዓተ ጉባኤ የሚሟላው ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸው ባለአክሲዮኖች ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ አንድ ሶስተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው እራሳቸው ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው ሲገኙ ነው፡፡
3. በመጀመሪያው ስብሰባ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ፣ ሁለተኛ ስብሰባ፤ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ሦስተኛ ስብሰባ በአንድ ሳምንት ልዩነት ውስጥ ይጠራል፡፡ የጉባዔውም ጥሪ በንግድ ህጉ በተደነገገው መሰረት ይሆናል፡፡
4. ሆኖም አስቸኳይ ጉባዔው በነባር አክሲዮኖች ላይ የተጻፈውን ዋጋ በመጨመር የማህበሩን ዋና ገንዘብ ለማሳደግ እንዲሁም የማህበሩን ዜግነት ለመለወጥ፣ ምልአተ ጉባኤ የሚሆነው ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው ሁሉም ጠቅላላ ባለአክሲዮኖች ሲገኙ ሆኖ ውሳኔውም የሚጸድቀው በሙሉ ድምፅ ሲደገፍ ብቻ ነው፡፡
5. በዚህ አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ 4 ላይ ከተጠቀሱት ውጭ ያለ አጀንዳ ላይ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡ ውሳኔዎች የሚፀድቁት በጉባዔዉ የተገኙት ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸዉ አክሲዮኖች ከወከሉት ካፒታል ሁለት ሦስተኛዉን በሚወክሉት ድምፅ ከተደገፈ ነዉ፡፡

## አንቀጽ 17

## የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ኃላፊነት

1. የማህበሩን መመስረቻ ጽሁፍ የማሻሻል፣
2. የማህበሩን ዋና ገንዘብ የማሳደግ ወይም የመቀነስ፣
3. የማህበሩን ዜግነት የመለወጥ፣

4. ማህበሩ እንዲፈርስ፣ ወደ ሌላ አይነት የንግድ ማህበር እንዲለወጥ፣ እንዲከፈል ወይም እንዲዋሃድ የመወሰን እና ሌሎች በሕግ ወይም በመመስረቻ ጽሁፍ በዚህ ጉባኤ እንዲታዩ ተለይተዉ የተሰጡትን ጉዳዮች የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

## አንቀፅ 18
## ወኪል ስለመሾም

1. የማህበሩ አክሲዮን የማይከፋፈል ነዉ፡፡
2. ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች የአክሲዮን የጋራ ባለቤት በሆኑ ጊዜ የባለአክሲዮንነት መብታቸዉን መጠቀም የሚችሉት የጋራ ወኪል በመሾም ነው፣ በጋራ ባለአክሲዮንነት ለሚመነጩ ሃላፊነቶች የጋራ ባለአክሲዮኖች በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡
3. አንድ ባለአክሲዮን በጉባዔዉ ስብሰባ ለይ የሚሳተፍ አንድ ተወካይ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት መወከል ይችላል፡፡ ይህም ተወካይ ያለዉ መብትና ግዴታ ከሌላዉ ባለአክሲዮን ጋር ተመሳሳይ ነዉ፡፡

## አንቀፅ 19
## የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ሃላፊነት

1. በህግ፣ በማህበሩ መመስረቻ ፅሁፍ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው በሚሰጠው መመሪያ መሰረት የዳይሬክተሮች ቦርድ የማህበሩን ስራ ይተገብራል፤ይመራል እንዲሁም ያስተዳድራል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 በአጠቃላይ ለዳይሬክተሮች ቦርድ የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣናት ይኖሩታል፡፡

   ሀ/ ዋና ስራ አስኪያጅ ይሾማል፣ ይሽራል፣ ደመወዝና አበሉን ይወስናል፡፡

   ሐ/ የማህበሩን ንብረቶች ሽያጭ፣ ግዥና በዋስትና የማስያዝ ሁኔታዎች ይወስናል፡፡

   መ/ የብድር፣ የቁጠባ አገልግሎት እና መሰል ሌሎች ፖሊሲዎችንና መመሪያዎች ያፀድቃል፡፡

   ሠ/ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎችን ይጠራል፡፡

   ረ/ የማህበሩን ለአደጋ ተጋላጭነት እና ውስጣዊ አሰራር ለመቆጣጠር የሚያስችል በቂ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል፡፡

   ሰ/ ዓመታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፡፡

   ሽ/ ከጠቅላላ ጉባኤ በሚሰጠው ውክልና መሰረት ማህበሩን በሚመለከት ማንኛውም ጉዳዩ ላይ ይወስናል፡፡

   ቀ/ ቦርዱን በሰብሳቢነት የሚያገለግል ከአባላቱ መካከል ይመርጣል፣ የሚመረጠው ሰብሳቢም የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባዎች ይመራል፡፡

በ/ ቦርዱ አስፈላጊ መስሎ በታየው ጊዜ ሁሉ ከአባላቱ መካከል ጉዳዮችን መርምረዉ የመፍትሄ ሃሳብ የሚያቀርቡ ኮሚቴዎችን ማቋቋም ይችላል፣እንደሁም ቦርዱ የሥልጣን ገደቡን ሳያልፍ የሚያቋቁማቸውን ኮሚቴዎች አባላት መምረጥ እና ሥልጣናቸዉን መወሰን ይችላል።

## አንቀፅ 20

## የዋናው ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ኃላፊነት

ማህበሩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ይኖረዋል። ዋናው ሥራ አስኪያጁ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የማህበሩን የቀን ተቀን ሥራዎችን ይመራል፣ ይቆጣጠራል።
2. የማህበሩን የባንክ ሂሳቦች ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣ይዘጋል አስፈላጊ ከሆነም ቦርዱ በሚሰጠው ዉክልና መሰረት የማህበሩን ሂሳብ በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል ወይም እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል፡
3. ከዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ብድሮችን ይፈቅዳል።
4. የማህበሩን ሰራተኞች አቀጣጠርና የአስተዳደር መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀርባል፣ ሲፀድቅ በሥራ ላይ ያውላል።
5. በፀደቀው መመሪያ መሰረት ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ በመመሪያው መሰረትም ከሥራ ያሰናብታል።
6. በየጊዜው የሥራ ክንውንና የሂሳብ ሪፖርቶችን ለቦርድ ያቀርባል።
7. ማህበሩን በመወከል በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ይደራደራል፣ ውሎችን ይፈርማል።
8. ማህበሩ ሲከስ ወይም ሲከሰስ ማህበሩን ወክሎ ፍርድ ቤት ይቀርባል፣ ወይም ህጋዊ ወኪል ወይም ጠበቃ መወከል ይችላል።
9. በዳይሬክተሮች ቦርድ ሲፈቀድ እንደ አስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን ይከፍታል።
10. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሲፈቅድ በማህበሩ ስም እንደ ባንክ ካሉና መሰል አበዳሪ ድርጅቶች ጋር ተደራድሮ የብድር ውል ስምምነት ይፈርማል፣ የማህበሩን የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት በዋስትና በማስያዝ ይበደራል፤ አፈፃፀሙንም በተመለከተ ለቦርዱ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል።
11. በማህበሩ ስም ተመዝግበው የሚገኙ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ይዘዉ ባሉት ዋጋ እስከ ብር አንድ ሚሊዩን ድረስ ለማህበሩ ጥቅም መሸጥ ወይም ማከራየት እንዲሁም ስመሃብታቸዉንም ወደ ገዥ ማዛወር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አፈጻጸሙን አስመልክቶ ለቦርዱ ዝርዝር ማብራሪያ ያቀርባል።

12. ዋና ስራ አስኪያጁ የተሰጠውን ስልጣን በከፊልም ሆነ በሙሉ በስሩ ላሉት የስራ ኃላፊዎች ወይም ለሌላ 3ኛ ወገን በውክልና መስጠት ይችላል፡፡
13. ዋና ሥራ አስኪያጁ ብቃት ያለውን አንድ የማህበሩን ፀሐፊ መርጦ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ቦርዱ ተቀብሎ ሲያፀድቀው በማህበሩ ፀሓፊነት ይመድባል፡፡
14. በዳይሬክተሮች ቦርድና በንግድ ሕጉ የተጣለበትን ሌሎች ተግባራቶችን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 21
## የማህበሩ ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባራት

የማህበሩ ፀሓፊ ተጠሪነቱ ለማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራትን ያከናውናል፡፡

1. የማህበሩን መረጃዎችንና መዛግብቶችን ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣ በአግባቡ መያዛቸዉንም ይቆጣጠራል፡፡
2. መረጃዎችንና መዛግብቶችን አስመልክቶ ለባለአክሲዮኖች፣ እና እንደአስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸዉ 3ኛ ወገኖች ጭምር መረጃዎችን ከደጋፊ ማስረጃዎች ጋር ይሰጣል፣ ሪፖርትም ያቀርባል፡፡
3. የባለአክሲዮኖችን እና የቦርድ አባላትን ስብሰባዎች ያዘጋጃል፣ ቃለጉባኤዎችንም ያዘጋጀል ፣ አደራጅቶም ይይዛል፡፡
4. በተጨማሪም ከዋና ሥራ አስኪያጁ እና በዚህ የመመስረቻ ጽሁፍ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡
5. የማህበሩ ፀሃፊ በዚህ የመመስረቻ ጽሁፍ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን በመተላለፍ በማህበሩ፣ በባለአክሲዮኖችና 3ኛ ወገኖች ላይ ለሚያደረሰው ጉዳት ሃላፊነት አለበት፡፡

## አንቀፅ 22
## ኦዲተር

1. ማህበሩ በጠቅላላ ጉባኤ የሚሾም የውጭ ኦዲተር ይኖረዋል፡፡
2. የኦዲተሩ የሥራ ዘመን የሶስት የሂሳብ ዓመት ሂሳብ ማጠቃለያ ጊዜ ነው፡፡
3. የኦዲተሩ የሥራ ግዴታዎችና ኃላፊነቶች በንግድ ህጉ በተደነገገው መሰረት ይሆናል፡፡

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

## አንቀፅ 23
## የሂሳብ አመትና ሪፖርት

1. የማህበሩ የሂሳብ አመት እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ ጁን 30 ይሆናል፡፡
2. የማህበሩ ዓመታዊ ሪፖርት የሂሳብ ዓመቱ እንዳለቀ በስድስት ወራት ጊዜ ዉስጥ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይቀርባል፡፡

## አንቀፅ 24
## ተፈፃሚነት ያላቸው ህጎች

በዚህ የማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ውስጥ ግልጽና የማያሻማ ሆኖ ያልተቀመጠ ጉዳይ ወይም ጉዳዮች በሙሉ በንግድ ህግና በሌሎችም ለጉዳዩ አግባብነት ባላቸው ህጎች፣ ደንቦችን መመሪያዎች መሰረት ይወሰናል፡፡

## አንቀፅ 25
## ማህበሩ የሚቆይበት ጊዜ

አክሲዮን ማህበሩ የተመሰረተው ላልተወሰነ ጊዜ ነው፡፡

ቡሳ ጎኖፋ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ

የባለአክሲዮኖች 10ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ

ሰኔ 3 ቀን 2015 ዓ.ም በተደረገዉ ጉባዔ ላይ የጉባኤው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet)

| ተ/ቁ | ስም ከነአያት | አድራሻ | | | | የአክሲዮኖች ብዛት | | | | የባለአክሲዮኑ ወይም የወኪሉ ስምና ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | ክ/ከተማ | ቀበሌ | የቤት ቁጥር | የተፈረመ | የተከፈለ | ያልተከፈለ | የድምፅ ቁጥር | |
| 1 | ሁንዴ- ኦሮሞ ግራስሩትስ ዴቬሎፐመንት ኢኒሼቲቭ | አዲስ አበባ | ቂርቆስ | ወረዳ-03 | 354 | 19,626 | 19,626 | የለም | 19,626 | |
| 2 | አቶ አለማየሁ ዲሮ ለሊሴ | አዲስ አበባ | ቦሌ | ወረዳ-04 | 335 | 18,692 | 18,692 | የለም | 18,692 | |
| 3 | አቶ አሸብር ከበደ ነገሮ | አዲስ አበባ | ቂርቆስ | ወረዳ-04 | 1080 | 467 | 467 | የለም | 467 | |
| 4 | ወ/ሮ ደራርቱ አባነጋ ሰዲቅ | አዲስ አበባ | --- | --- | 332/21 | 467 | 467 | የለም | --- | የቀረ (Absentee) |
| 5 | አቶ ደረጀ ካሳ አብዲ | ኦሮሚያ | ሞጆ | ቀ-02 | 2118 | 467 | 467 | የለም | --- | የቀረ (Absentee) |
| 6 | ዶክተር ገመቹ መገርሳ ሩዳ | አዲስ አበባ | --- | ወረዳ-14 ቀ-07 | C-201 | 18,692 | 18,692 | የለም | --- | የቀረ (Absentee) |
| 7 | ወ/ሮ ገነት ታደሰ ዱባለ | አዲስ አበባ | --- | --- | አዲስ | 192 | 192 | የለም | --- | የቀረ (Absentee) |
| 8 | ወ/ት ቁንቢ ኩምሳ ቦሮ | አዲስ አበባ | --- | --- | 785 | 467 | 467 | የለም | --- | የቀረ (Absentee) |
| 9 | አቶ መንግስቱ ያዕቆብ ጉደታ | አዲስ አበባ | ቦሌ | ወረዳ-10 | 202A | 234 | 234 | የለም | 234 | |
| 10 | ወ/ሮ ሸምሲያ አስማን መሐመድ | አዲስ አበባ | ንፋስ/ስልክ ላፍቶ | ወረዳ-12 | 3905 | 467 | 467 | የለም | 467 | |
| 11 | አቶ ሶርሳ ደበላ ገላልቻ | አዲስ አበባ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን | ቡራዩ | ቡራዩ ከታ | 4937 | 467 | 467 | የለም | 467 | |
| 12 | አቶ ተርፌሳ ደንደና ጉተማ | አዲስ አበባ | ቦሌ | ወረዳ-05 | 1506 | 467 | 467 | የለም | 467 | |
| 13 | አቶ ተስፋዬ ደስታ ክ/ሚካኤል | አዲስ አበባ | ቂርቆስ | ወረዳ-05 | አዲስ | 467 | 467 | የለም | 467 | |
| 14 | አቶ ተሾመ ዮሐንስ ደዬሶ | አዲስ አበባ | አቃቂ-ቃሊት | ወረዳ-01 | 772 | 18,692 | 18,692 | የለም | 18,692 | |
| 15 | ወ/ት ትዕግስት ታደሰ ዱባለ | አዲስ አበባ | --- | --- | 257 | 234 | 234 | የለም | --- | የቀረ (Absentee) |
| 16 | አቶ ዘገየ አሰፋዉ አብዲ | አዲስ አበባ | ቦሌ | ወረዳ-03 | 207 | 19,626 | 19,626 | የለም | 19,626 | |
| 17 | አቶ እንዳለ ፎዬ ጂሩ | አዲስ አበባ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን | ቡራዩ | ለኩ ከታ 02 | 8625 | 138 | 138 | የለም | 138 | |
| 18 | አቶ ሰለሞን ማሞ አረዶ | አዲስ አበባ | ንፋስ/ስልክ ላፍቶ | ወረዳ-01 | አዲስ | 138 | 138 | የለም | 138 | |
| | ድምር | | | | | 100,000 | 100,000 | | | |

እኔ የቡሳ ጎኖፋ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር ፀሐፊ ይህ የጉባኤ ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet) በጉባኤው በአካል የተገኙ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎች የፈረሙበት ስለ መሆኑን በሙሉ ስም እና ፊርማዬ በንግድ ህግ አንቀፅ (378(2) መሰረት አረጋግጣለሁ፡፡

ፀሐፊ ስም፡ ________________

ፊርማ፡ ________________

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት
ቅ/10 ጽ/ቤት አ/አ
ፊርማው የጽ/ቤቱ ቀርበው ፊርመዋል፡፡
ቁጥር ቅ10/OD3318/4ህ/16
11/7/2016

Jemal Haji Kedir
Document Authentication &
Registration Expert IV